**ፕሪሚየር ስዊች ሶሉሽንስ አክሲዮን ማህበር**
**የባለአክሲዮን 3ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ**
**ቃለ ጉባዔ ቁጥር 03/2015**

1. **ጠቅላላ ጉባዔው የተደረገበት ቦታ፣ ቀንና ሰዓት**

- ቦታ፡- አዲስ አበባ ሒልተን ሆቴል
- ቀን፡- ሕዳር 1 ቀን 2015ዓ.ም.
- ሠዓት፡- 10፡30

2. **የጉባዔው ጥሪ አደራረግ**

ይህ የባለአክሲዮኖች 3ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የተጠራው በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 367 እና 370 መሠረት ሆኖ ከጉባዔው ዕለት 24 ቀናት አስቀድሞ በሪፖርተር ጋዜጣ መስከረም 29 ቀን 2015 ዓ.ም. እና ጥቅምት 9 ቀን 2015 ዓ.ም. እትም ተጠርቷል፡፡

3. **የጉባኤው ድምጽ ቆጣሪዎች ስለመሰየም እና በጉባኤው የተገኙ ዳይሬክተሮች**

3.1. **የጉባኤው ድምጽ ቆጣሪዎች**

በንግድ ሕጉ አንቀጽ 380/1 መሰረት በጉባኤው በባለአክሲዮንነት ወይም በወኪልነት ከተገኙ እና ፍቃደኛ ከሆኑት ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ባላቸው ባለአክሲኖች መካከል በተደረገ ስምምነት ከዚህ በታች ስማቸው የተዘረዘረው የጉባኤው ድምጽ ቆጣሪዎች ሆነው ተመርጠዋል፡፡

| ቁ | ስም | የተወካይ ስም |
|---|---|---|
| 1. | አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ | አቶ ዮሐንስ መርጋ ጉዲና) |
| 2. | ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ. | አቶ ገነነ ሩጋ ተሊላ |

3.2. **በጉባኤው የተገኙ የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት**

| ቁ | ስም | ኃላፊነት | የተወካይ ዳይሬክተር ስም (ካለ) |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ፀሐይ ሽፈራው ኢንሰርሙ | ሊቀመንበር | |
| 2 | አቶ ሰለሞን ጎሽሜ | አባል | |
| 3 | አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ. | አባል | አቶ ዮሐንስ መርጋ ጉዲና |
| 4 | ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ. | አባል | አቶ ገነነ ሩጋ ተሊላ |
| 5 | አዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ. | አባል | አቶ ሐይሉ አለሙ |
| 6 | ሕብረት ባንክ አ.ማ. | አባል | አቶ መላኩ ከበደ እሸቴ |

3.3. **በጉባኤው ያልተገኙ የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት**

| ቁ | ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1. | አቶ ታዬ ዲበኩሉ | አባል |

3.4. በጉባዔው የተገኙ ታዛቢዎች

| ቁ | ስም | የወከሉት ድርጅት |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌቱ ዘሪሁን | ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ |
| 2 | አቶ ቢቂላ ወርቅነህ | ከፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት |

4. **ምልዓተጉባኤ**

- ጠቅላላ የማኅበሩ አባላት ብዛት 21
- ጠቅላላ የማህበሩ የተፈረመ አክሲዮን ብዛት 165,001
- ጠቅላላ የማኅበሩ የተከፈለ አክሲዮን ብዛት149,403
- በስብሰባው የተገኙ አባላት ብዛት 16
- በስብሰባው የተገኙ አባላት ብዛት የያዙት አክሲዮን ብዛት 160,197 (97.1%)
- በስብሰባው ያልተገኙ አባላት ብዛት የያዙት አክሲዮን ብዛት 4,804 (2.9 %)
- ለጉባኤው አስፈላጊ የሆነ የአክሲዮን ብዛት 55,000.33 (33.33%)

በዚሁ መሠረት በንግድ ህጉ አንቀጽ 402 መሠረት ከአክሲዮን ማኅበሩ ባለአክሲዮኖች 97.1% የሚወክሉ አባላት የተገኙ ስለሆነ በጉባኤው አጀንዳ ላይ ተወያይተው ውሳኔን ማሳለፍ ሥልጣን ያላቸው መሆኑ በድምፅ ቆጣሪዎች ተረጋግጦ ጉባዔው ቀጥሏል፡፡ በጉባኤው ላይ የተገኙትን እና ያልተገኙትን ባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝርና የያዙትን አክሲዮን መጠን የያዘ የጉባዔው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance Sheet) ሰንጠረዥ-1 ከዚህ ቃለጉባዔ ሰነድ ጋር ተያይዟል፡፡

5. **የጉባዔውአጀንዳዎች**

1. የጉባዔውን አጀንዳ ማፅደቅ፣
2. የማኅበሩን መመሥረቻ ጽሑፍ ማሻሻል
3. የማኅበሩን ካፒታል ማሳደግ
4. የስብሰባውን ቃለጉባኤ ማጽደቅ፡፡

6. **የጉባዔው ውይይት አጭር ቃልና ውሳኔ**

6.1 **የጉባዔውን አጀንዳ ማፅደቅ**

ጠቅላላ ጉባዔው የስብሰባውን አጀንዳ እንደቀረበ በሙሉ ድምፅ አጽድቋል፡፡

6.2 **አጀንዳ 2. የማኅበሩን መመሥረቻ ጽሑፍ ማሻሻል**

**ሀ. የውይይቱ አጭር ቃል**

የጉባዔው ሰብሳቢ የማኅበሩን መመሥረቻ ጽሑፍ ማሻሻል ያስፈለገበትን ምክንያት ሲያስረዱ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚጠራበት ጊዜ በመመሥረቻ ጽሑፍ እስከስድስት ወራት ማራዘም የሚቻል በመሆኑና የማኅበሩ ዳይሬክተሮች ቦርድ የስብሳባ መጥሪያውን ጊዜ ማራዘሙ አስፈላጊነቱን እና የማኅበሩ ሥራ እየሰፋ በመምጣቱና ቦርዱ ሥራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመምራት የዳይሬክተሮችን ቁጥር ማሳደግ ተገቢ መሆኑን ገልጠው በውሳኔ ሀሳቡ ላይ ውይይት እንዲደረግበት ጋብዘዋል፡፡

ይሁን እንጂ በውሳኔ ሀሳቡ ላይ የተነሳ ጥያቄም ሆነ አስተያየት ባለመኖሩ በአጀንዳው ላይ የተደረገው ውይይት በዚሁ አበቃ፡፡

**ለ. ውሳኔ**

በአጀንዳው ላይ ጥያቄና አስተያየት ባለመኖሩ ባለአክሲዮኖች እጅ በማውጣት ድምፅ እንዲሰጡ ተደርጎ የማኅበሩን የመመሥረቻ ጽሑፍ ለማሻሻል የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ያለምንም ተቃውሞ እና ደምፀ ተዓቅቦ በስብሰባው በተገኙት ባለአክሲዮኖች ሙሉ ድምፅ ፀድቋል፡፡ በመሆኑም የማኅበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

1. በማኅበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ **አንቀጽ** 10 ሥር የሚከተለው ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 4 ሆኖ ገብቷል፡-

   "የማኅበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በየዓመቱ የሒሳብ ዓመት ከተዘጋበት ቀን ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ መካሄድ **አለበት**" "the ordinary general meeting shall be held annually within six months from the end of each financial year"

2. የማኅበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ **አንቀጽ** 11.2 **እንደሚከተለው** ተሻሽሏል፡-

   "የማኅበሩ አስተዳደር 9 አባላት ባሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ ይመራል። የዳይሬክተሮች ቦርድ በንግድ ሕጉ ለጠቅላላ ጉባዔ ወይም ለሌላ አስተዳደር አካላት ተለይቶ ከተሰጠ ሥልጣን ውጪ ማኅበሩን ለመምራትና ለማስተዳደር ሙሉ ሥልጣን ይኖረዋል" "The business of the Company shall be managed by the Board of Directors consisting of 9 Directors who shall exercise all such powers of the Company except for those powers reserved to the general meeting of shareholders or other organs of the Company by the Commercial Code of Ethiopia"

## 6.3አጀንዳ 3. የማኅበሩን ካፒታል ማሳደግ

### ሀ. የውይይቱ አጭር ቃል

የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር እና ጉባዔው ሰብሳቢ ማኅበሩ የተመሰረተው በ30 ሚሊዮን ብር ካፒታል መሆኑ እና ጥቅምት 6 ቀን 2004 ዓ.ም. በተደረገው 1ኛው የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የማኅበሩን ካፒታል ወደ 165 ሚሊዮን አንድ ሺህ ብር ከፍ እንዲል መወሰኑን አስታውሰው በዚሁ መሠረት ተጨማሪ የወጡት አክሲዮኖች ሙሉ ለሙሉ ተፈርመው የተፈረመው ካፒታል 165 ሚሊዮን አንድ ሺህ ብር ከፍ ያለ ሲሆን የተከፈለው ካፒታል ደግሞ ብር 149,402,000.00 መድረሱን ገልፀዋል። በመቀጠል የኩባንያውን ሕልውና ለማረጋገጥና ትርፋማነቱን ለማሳደግ ካፒታሉን ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን እና ካፒታሉን ለማሳደግ ዋና ዋና ምክንያቶቹን የዘረዘሩ ሲሆን እነሱም

1. ማኅበሩ ለረዥም ጊዜ ሲጠቀምበት የቆየው የክፍያ ሥርዓት ስዊች (payment system switch) እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት (IT infrastructure) መቀየር እና ዘመኑ የሚጠይቀውን ሁሉን አቀፍ የክፍያ ሥርዓት (omni channel payment system) መተግበር እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ማሻሻል (IT infrastructure upgrading) አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤
2. በ5 ዓመት ስትራቴጂ ዕቅድ መሠረት አዳዲስ ምርትና ለማስተዋወቅ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መተግበር ግድ የሚል በመሆኑ፤ እና
3. በ5 ዓመት ስትራቴጂ ዕቅድ መሠረት የማኅበሩን ገቢ ለማሳደግ እህት ኩባንያ አቋቁሞ በተለያዩ ተያያዥና አዋጭ የሥራ ዘርፎች ለመሰማራት ከፍተኛ የካፒታል ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑና ይህንን ተጨማሪ ወጪ ማኅበሩ ባለው ሀብት ብቻ መሸፈን የማይቻል በመሆኑ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

በዚሁ መሠረት አዳዲስ አክሲዮኖች ከመውጣታቸው በፊት የማኅበሩ የተፈረመ ካፒታል ብር 165,001,000.00 (አንድ መቶ ስድሳ አምስት ሚሊዮን አንድ ሺህ ብር) ሙሉ ለሙሉ መከፈላቸውን የዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲያረጋግጥ ሥልጣን ተሰጥቶት ካረጋገጠ በኃላ ተጨማሪ 231,400 አዳዲስ መደበኛ አክሲዮኖችን በማውጣት የማኅበሩ ካፒታል ከብር 165,001,000.00 (አንድ መቶ ስድሳ አምስት ሚሊዮን አንድ ሺህ ብር) ወደ ብር 396,401,000.00 (ሦስት መቶ ዘጠና ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ አንድ ሺህ ብር) ከፍ እንዲል እና ዝርዝር አፈፃፀሙን በተለመከተ ለዲሬክተሮች ቦርድ ሥልጣን እንዲሰጠው የውሳኔ ሀሳብ መቅረቡን ገልጠው መድረኩን ለውይይት ከፍተዋል፡፡

በዚሁ መሠረት ከባለአክሲዮኖች የካፒታል መጠኑ ለምን 396 ሚሊዮን እንዲሆን ተፈለገ? ለምን ከፍ ወይም ዝቅ አላለም? ተያያዥ የንግድ ሥራዎች በሚል የሚገለፁት ምንድን ናቸው? ከሚወጡት አዳዲስ አክሲዮኖች ባለአክሲዮኖች በቅድሚያ የመግዛት መብታቸው እስከምን ድረስ ይጠበቃል? የሚሉ ጥያቄዎች ተነስቷል፡፡

ለቀረቡት ጥያቄዎች ከመድረኩ መልስ ተሰጥቷል፡፡ የካፒታል ጭማሪው መሠረት ያደረገው ድርጅቱ አሁን ያለውን የገንዘብ አቅም፣ በቀጣይ ዓመታት ለመሥራት ያቀዳቸውን ግዙፍ የመሠረተ ልማት (switch system & IT Infrastrucure) እና የባለአክሲዮን ባንኮችን አቅም መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ተያያዥ የንግድ ሥራዎች የተባሉት አክሲዮን ማኅበሩ በዋናነት ከተቋቋመበት የክፍያ ሥርዓት አከናዋኝነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው እንደክፍያ ካርድ

አስመጥቶ ማተም (import and personalization of payment cards፣ የክፍያ መፈፀሚያ ማሽን (Import of POS terminals) ማስመጣት የመሳሰሉት ሲሆን በአክሲዮን ማኅበሩ የአምስት ዓመት ዕቅድ መሠረት እህት (subsidiary)ኩባንያ በማቋቋም በዘርፉ ለመሠማራት መታሰቡ ተገልጧል፡፡ የባለአክሲዮኖች የቅድሚያ መብትን በተመለከተ ሙሉ በሙሉ የሚፈፀመው በንግድ ሕጉ መሠረት መሆኑን ተመልክቶ ለማኅበሩ ጥቅም ሊሰጡ ለሚችሉ አካላት አክሲዮን ሊሸጥ የሚችለው በሕጉ መሠረት ነባር ባለአክሲዮኖች በሕግ የተሰጣቸውን በቅድሚያ የመግዛት መብት ካልተጠቀሙበት ብቻ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በአጀንዳ ላይ የተነሳ ተጨማሪ ጥያቄም ሆነ አስተያየት ባለመኖሩ በአጀንዳው ላይ የተደረገው ውይይት በዚሁ አበቃ፡፡

**ለ. ውሳኔ**

በአጀንዳው ላይ የተደረገው ውይይት ከተጠናቀቀ በኃላ ባለአክሲዮኖች እጅ በማውጣት ድምፅ እንዲሰጡ ተደርጎ የማኅበሩን ካፒታል ለማሳደግ የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ያለምንም ተቃውሞ እና ደምፀ ተዓቅቦ በስብሰባው በተገኙት ባለአክሲዮኖች ሙሉ ድምፅ ፀድቋል፡፡ በመሆኑም፡-

1. አዳዲስ አክሲዮኖች ከመውጣታቸው በፊት የማኅበሩ የተፈረመ ካፒታል ብር 165,001,000.00 (አንድ መቶ ስድሳ አምስት ሚሊዮን አንድ ሺህ ብር) ሙሉ ለሙሉ መከፈላቸውን እንዲያረጋግጥ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣን ተሰጥቶታል፤
2. ተጨማሪ 231,400 አዳዲስ መደበኛ አክሲዮኖችን በማውጣት የማኅበሩ ካፒታል ከብር 165,001,000.00 (አንድ መቶ ስድሳ አምስት ሚሊዮን አንድ ሺህ ብር) ወደ ብር 396,401,000.00 (ሦስት መቶ ዘጠና ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ አንድ ሺህ ብር) ከፍ እንዲል ተወስኗል፤
3. የአዳዲስ አክሲዮኖች ሽያጭ ቦርዱ የማኅበሩ የተፈረመ ካፒታል ሙሉ ለሙሉ መከፈሉን ካረጋገጠበት ቀን ጀምሮ የሦስት ዓመታት ክፍት ሆኖ እንዲቆይ ተወስኗል፤
4. የካፒታል ጭማሪውን አፈፃፀም፥ ነባር ባለአክሲዮኖች አዳዲስ ከሚወጡት አክሲዮኖች ባላቸው አክሲዮን ልክ በቅድሚያ የመግዛት መብታቸው የሚጠበቅበት ሁኔታና የጊዜ ገደብ፥ ባለአክሲዮኖች የቅድሚያ መብታቸውን ተጠቅመው የተረፈ አክሲዮን የሚሸጥበትን ሁኔታ፥ ክፍያ የሚጠናቀቅበትን ጊዜና የመሳሰሉትን የማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲወስን ሥልጣን ተሰጥቶታል

**6.4አጀንዳ 8-የስብሰባውን ቃለጉባዔ ማፅደቅ**

ስብሰባው ከተጠናቀቀ በኃላ ቃለጉባዔው በማኅበሩ ፀሐፊ ከተነበበ በኃላ ማስተካከያ ተደርጎበት ጉባዔው በስብሰባው በተገኙት ባለአክሲዮኖች በሙሉ ድምፅ አፅድቋል፡፡

7. **ለጉባዔው የቀረቡ ሰነዶች**

7.1. የማኅበሩን መመሥረቻ ለማሻሻል የቀረበ የውሳኔ ሀሳብ፤ እና
7.2. የማኅበሩን ካፒታል ለማሳደግ የቀረበ የውሳኔ ሀሳብ፤

8. <u>የአክሲዮን ማኅበሩ ዳይሬክተሮች እና የጉባዔው ጸሐፊ ማረጋገጫ</u>

እኛ የፕሪሚየር ስዊች ሶሉሽንስ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትና ጸሐፊ ሕዳር 1 ቀን 2015 ዓ.ም. በተካሄደው የአክሲዮን ማኅበሩ 3ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የተያዘው በትክክል ስለመመዝገቡ በንግድ ሕግ አንቀጽ 387 (1) መሠረት በሙሉ ስምና ፊርማችን እናረጋግጣለን፡፡

| ቁ | ስም | ተወካይ | ኃላፊነት | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ፀሐይ ሽፈራው ኢንስርሙ |  | ሰብሳቢ |  |
| 2 | ሕብረት ባንክ አ.ማ. | አቶ መላኩ ከበደ እሸቱ | ዲሬክተር |  |
| 3 | አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ. | አቶ ዮሐንስ መርጋ ጉዲና | ዲሬክተር |  |
| 4 | አዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ. | አቶ ኃይሉ አለሙ | ዲሬክተር |  |
| 5 | ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ | አቶ ገነነ ሩጋ ተሊላ | ዲሬክተር |  |
| 6 | አቶ ሰለሞን ኀሽሜ በጂጋ |  | ዲሬክተር |  |
| 7 | አቶ ኤፍሬም ኃ/ማርያም በዛብህ |  | የማኅበሩ ጸሐፊ |  |

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት
ቅ/10 ጽ/ቤት አ/አ
ፊራሚው በጽ/ቤቱ ቀርበው ፈርመዋል፡፡
ቁጥር ቅ10/መመ6050/ቁ11/2015
ቀን 22/6/2015

Bikila Workineh Negasa
Document Authentication and Registration

Documents Authentication & Registration Service Branch 10 Office

የሰነዶች ማረጋገጫና
ምዝገባ አገልግሎት
አዲስ አበባ (የቅርንጫፍ አስር ጽ/ቤት)

የቴምብር ቀረጥ ማረጋገጫ ማህተም

የክፍያው ምክንያት ___ ውክልና
የገቢ ልክ ቁ፡ ___
ክፍያ ___
ደረሰኝ ቁ፡ ___ ያለ ቴምብር ተከፍሏል ፡፡ 3805317
የደረሰኝ ቁጥር ___
22/06 ቀን 20 15
የቴምብር ቀረጥ መብት አስፈፃሚ
ስም ___
ፊርማ ___